## 1.መግቢያ

በክልላችን ልማትን መልካም አስተዳደርን በማስፈን ግልጽና ተጠያቂነትን ሊያመጣ የሚችል የአሰራር ሂደትና ሥርዓት በመዘርጋት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም መሰረት የክልሉን ልማታዊና ኢኮኖሚያዊ ዕቅዶችን የሚያስፈጽሙ ሴክተሮች ተቋቁመው የዕድገትና ትራንፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳከትና ፈጣን ልማትን ለማረጋገጥ በመረባረብ ላይ ይገኛሉ፡፡

በክልላችን ከተቋቋሙት ቢሮዎች ውስጥ አንዱ የንግድ ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ሴክተር ሲሆን ከተልዕኮውም አንዱ የንግዱን ዘርፍ ማስፋፋትና ህጋዊነትን ማስፈን ነው፡፡ ሆኖም ግን በአሁኑ ወቅት ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያመለክተው የንግዱ ዘርፍ እጅግ ኋላ ቀር የሆነ እና ውስብስብ ችግሮች የሚስተዋልበት ከመሆኑም በላይ የተለያዩ ሕገወጥ ተግባራት የሚከናወንበትና ለነጻ ውድድር ምቹ ያልሆነ ሆኖ ይገኛል።
ይህን ሁኔታ መሰረታዊ በሆነ መልኩ ለመቀየር መንግስት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ እንዲሁም የንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅን አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ እንገኛለን። እነዚህ አዋጆች በመውጣታቸውና ተግባራዊ መሆን በመጀመራቸው አበረታች ውጤቶች በመመዝገብ ላይ ያሉ ሲሆን በንግድ ስርዓቱ ውስጥ የሚታየው ችግር ለዘመናት የተከማቸና የተወሳሰበ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ የህግ ማዕቀፍ አውጥቶ በመተግበር ብቻ የሚቃለል ሳይሆን መሰረታዊ በሆነ መልኩ የስርዓት ለውጥ ማምጣትን የሚጠይቅ ነው።
ይህን መሰረታዊ የሆነ ሁሉ አቀፍ ለውጥ ለማምጣት የተሟላ የለውጥ ፕሮግራም መንደፍ በማስፍለጉ የንግድ ስርዓት ሪፎርም ፕሮግራም ተቀርጾ በክልሉ መንግስት ጸድቋል።
ፕግራሙንም ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አጣጥሞ ለመተግበር በ2000 ዓ/ም ተጠንቶ ተግባራዊ የተደረገው የስራ ሂደት አደረጃጀት ምቹ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህም ባሻገር ነባሩ የስራ ሂደት በውስጡ በርካታ ተግባራትን አጠቃሎ የያዘ ስለነበረ በሚፈለገው ደረጃ የነበረዉንም ሥራ ውጤታማ ማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም የጸደቀዉን የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራም በተሳለጠ ሁኔታ በመተግበር በንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት እና ዘርፉ በሀገሪቱ ፈጣን የልማት ዕድገት የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ ማበርከት እንዲችል ነባሩን የሥራ ሂደት አደረጃጀት በአዲስ መልክ መቅረጽ ግድ ይላል።

ስለሆነም የንግድ ምዝገባ አፈፃፀምና የንግድ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን ለማራመድና ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ለማምጣት በሚያስችል መልኩ እንዲሻሻል ለማድረግ፣የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ሥራዎችን እና የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ሥራዎችን በተገቢው መንገድ ለማከናወን በሚያስችል አደረጃጀት በ 4 ዋና የስራ ሂደት እንዲቀረጽ ተደርጓል ፡፡

የስራ ሂደቶቹም፤

1. የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት
2. የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት
3. የገበያ ልማትና የግብይት አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት
4. የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት

ናቸው፡፡

## 2.የጥናቱ አስፈላጊነት እና ዓላማ

### 2.1 የጥናቱ አስፈላጊነት

በ2000 ዓ/ም መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ተጠንቶ ተግባራዊ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ዘመናዊ የንግድ ሥርአትን በክልሉ ለመዘርጋት የተደረገው ጥረት ይበል የሚሰኝ ቢሆንም በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ በነበረው የተዛባ አመለካከት በንግድ ስርዓቱ ላይ የሚጠበቀው ውጤት ሊመጣ እንዳልቻለ የሚታወቅ ነው፡፡ ለውጤቱ ያለመምጣት በዋናነት የንግዱ ሥርዓት እንደ ሀገር በበርካታ ችግሮች ተተብትቦ የኖረ መሆኑ ሲሆን በክልላችንም በተመሳሳይ ሁኔታ የንግድ ሥርዓቱ ከፍተኛ ችግሮች ነበሩበት፡፡ ከበርካታ ችግሮች መካከል የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎች፣ የኢንስፔክሽንና የእርምጃ አወሳሰድ፣ የሸማቾች መብትና ጥቅም አለመከበር እንዲሁም የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት ደካማ መሆን እና የመሳሰሉት ስር የሰደዱ ችግሮች ናቸው፡፡እነዚህንም ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል የንግድ ሥርዓት ሪፎርም የተቀረጸ ሲሆን ለመተግበር ነባሩ የሥራ ሂደት አደረጃጀት ምቹ ካለመሆኑም በላይ በውስጡ በርካታ ተግባራትን አጠቃሎ የያዘ ስለነበረ ይህንን የመሰረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ /BPR/ ጥናት መስራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 2.2 የጥናቱ ዓላማ

□ጥናቱ ዋና ዓላማ የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራምን ለመተግበር የሚያስችል ዘመናዊ አደረጃጀት በመፍጠር በንግዱ □ር□ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣውን የንግዱንና ሸማቹን ህብረተሰብ ፍላጎት ለማርካት፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ዘርፉን ተ□□ሪ እንዲሆን በሚያስችል መልኩ የስራ ሂደቱን በአዲስ አደረጃጃት በመቅረጽ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፡፡

## 3. ተልዕኮ

### 3.1የሴክተሩ ተልዕኮ

ኢንተርፐርይዞችን በማስፋፋት ለዜጎች የስራ ዕድልን በመፍጠር የኢንቨስትመንት ኢንዱስትሪ ልማትን በማፋጠን ህጋዊ የንግድ ስርዓትን በማስፈን በፕላን የሚመሩ የከተሞች ልማትና የከተማ መሬት አቅርቦትን ቀልጣፋ በክልሉ ልማትና መልንም አስተዳደርን ማረጋገጥ ነዉ፡፡

### 4.2 የተቋሙ ተልዕኮ

ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ ልማትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ፡፡

### 4.ራዕይ

### 4.1የሴክተሩ ራዕይ

የክልሉ ከተሞች ለኑሮና ኢንቨስትመንት ምቹ ሆነው ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥሩ ተቋማት ተስፋፍተው ህጋዊ ንግድ ሰፍኖ በ2012 ዓ/ም ኢንዱስትሪ የክልሉ ኢኮኖሚ መሪ ሆኖ ማየት ፡፡

### 4.2 የተቋሙ ራዕይ

ዘመናዊ የንግድና የግብይት አሰራር ተስፋፍቶ፤ህጋዊና ፍትሃዊ ንግድ ሰፍኖ በ2012 ዓ/ም የንግዱ ዘርፍ ለክልሉ ኢኮኖሚ ዕድገት ዋነኛ ምንጭ ሆኖ ማየት፡፡

## 5.ዓላማ

### 5.1 የሴክተሩ ዓላማ

በሴክተሩ ቀጣይነትና ዘለቄታዊነት ያለው ልማት ለማረጋጥ የሚያስችል የአሰራር ሂደቶችን በመዘርጋት እንዲሁም ተመጋጋቢ የሆኑ የስራ ሂደቶችን በማጣመር የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን ቀልጣፋና ተደራሽ በማድረግ የተገልጋዩን ህብረተሰብ ፍላጎት ማርካት ነው፡፡

### 5.2 የተቋሙ ዓላማ

በተቋሙ ቀጣይነትና ዘላቂነት ያለው ህጋዊና ፍትሃዊ ንግድን ለማስፈን የሚያስችሉ የአሰራር ሂደቶችን በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጥ ስርዓቱን ቀልጣፋና ተደራሽ በማድረግ የተገልጋዩን ህብረተሰብና ባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ማርካት ነው፡፡

### 6.በተቋሙ የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች

☞ በንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ሥራዎች

- የንግድ ስም ምዝገባ
- የንግድ ምዝገባ ማድረግና ፈቃድ መስጠት
- ንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዕድሳት ማድረግ
- የንግድ ተቋም ዋስትና መያዣ ምዝገባ

- የንግድ ማህበራት የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደርያ ደንብ እና ቃለ ጉባዔ ማፅደቅ
- ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎችን መቀበልና ምላሽ መስጠት
- በንግድ ምዝገባና ፈቃድ  የአቅም ግንባታና ኮሚኒኬሽንና ስራዎች  ማከናወን
- በንግድ ምዝግባና ፈቃድ አገልግሎት ጥናት ማካሄድ

**የንግድ መረጃ አገልግሎት**

- የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዳታ ቤዝ በማዘጋጀት መረጃ ማስገባትና ማደራጀት መተንትንና ማሰራጨት
- የንግድ ስም ፣ምዝገባና ፈቃድ መረጃዎችንና የአገልግሎት አሰጣጥ ቅድመ ሁኔታዎችን በመረጃ መረብ መሰደርና ለተጠቃሚው ማቅረብ
- የቅድመ ምዝገባና ፈቃድ የምክር አገልግሎት

☞ ***የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ  ሥራዎች***

**የኢንስፔክሽን አገልግሎት**

- ***ውስጣዊ  የኢንስፔክሽን አሰራር***
  - የንግድ ስም አገልግሎት አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ምዝገባና ዕድሳት አገልግሎት አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - የፈቃድና ዕድሳት አገልግሎት አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ተቋም ዋስትና መያዣ ምዝገባ ስራዎች አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ማህበራት የመመስረቻ ጽሁፍና መተዳደርያ ደንብ እና ቃለ ጉባዔ  የማፅደቅ ስራዎች አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - ከንግድ ምዝገባና ፈቃድ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎችን የመቀበልና ምላሽ የመስጠት ሥራዎች አፈጻጸም ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ስም ፣ምዝገባና ፈቃድ መረጃዎችና የአገልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ኢንስፔክሽን

- ***ውጫዊ የኢንስፔክሽን አሠራር***
  - የንግድ ምዝገባ ሳያደርጉና ፈቃድ ሳያወጡ የንግድ ስራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች፣ማህበራትና ተቋማት ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን
  - የተሰጠ የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድና እድሣት በአግባቡ ሥራ ላይ ስለመዋሉ የሚደረግ ኢንስፔክሽን
  - በፈቃድ መስጫ መደብ በተሰጠው የንግድ ሥራ ፈቃድ መሠረት በማይነግዱት ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ፈቃድ በግልጽ በሚታይ ቦታ ስለመለጠፉና የሚደረግ ኢንስፔክሽን
  - ምዝገባ ሲደረግና ፈቃድ ሲሰጥ በነጋዴው /በማህበሩ የተሰጡ መረጃዎች ትክክለኛነት በመስክ የማረጋገጥ ኢንስፔክሽን
  - የስነልክ መሳሪያዎች ተመርምረው ማራጋገጫ የተሠጠ ስለመሆኑ የሚደረግ ኢንስፔክሽን
  - የንግድ ኢንስፔክሽን ጥናታዊ ስራዎች
  - የስልጠናና የኮሚኒኬሽን ስራዎች

**የሬጉላቶሪ ስራዎች**

- የህግ ማእቀፎች ማዘጋጀት ማስተባበርና አፈፃፀማቸውን መከታተል
- የቴክኒክ ደንቦች ማስተባበር/የፈቃድ መስጫ መደቦች መስፈርቶችን የሚያወጡና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጡ አካላትን ማስተባበር /
- የምርትና የአገልግሎት ጥራትና ደረጃ ፍተሻ ማድረግና ህጋዊ ማስተካከያና እርምጃና መውሰድ
- የልኬት መሳሪያዎች ካልብሬሽንና ፍተሻ ማድረግ፤ ተገቢውን ማስተካከያ ማድረግና እርምጃ መውሰድ
- የምርቶችና አገልግሎቶች አቅርቦት ችግሮች የመለየትና ማስተካከያ እርምጃ የመውሰድ ስራዎች
- የነዳጅ ማደያዎች የምርት ጥራት፣ ስርጭትና አግልግሎት ህጋዊነት ማረጋገጥ
- የንግድ ስራዎችና አገልግሎቶች ከአካባቢ ብክለት የማያስከትሉ መሆኑን መከታተልና ተገቢውን ማስተካከያ እርምጃ መውሰድ

- የንግድ ሬጉላቶሪ ጥናታዊ ስራዎች
- የስልጠናና የኮሚኒኬሽን ስራዎች

☞ **የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ስራዎች**

***የትምህርት፣የስልጠናና የድጋፍ ስራዎች***

- የሸማቾችን ግንዛቤ ለማዳበርና መብቱን ለማስከበር የሚያስችለውን ትምህርትና ሥልጠና መስጠት
- ነጋዴዎች ለሸማቹ በህግ የተሰጡ መብቶችን እንዲያከብሩ ና የራሳቸውን ግዴታ መወጣት እንዲችሉማሰልጠን
- አዋጆችን ደምቦችንና መመሪያዎችን ለሸማቾች፤ለነጋዴዎች እና ለባለድረሻ አካላት ማሰልጠን
- ለሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት በሸማቾች መብት ላይ ስልጠና መስጠት
- የሸማቾችን ተሳትፎ የማሳደግ ስራዎች
- የሸማቹን ህብረተሰብ የመደራደርና ለመብቱ የመቆም አቅም የማሳደግ ስራዎች
- የሸማቾች ህብረት ሥራ ማህበራትን አቅም የመገንባት፣ የመደገፍና የገበያ ትስስር የማስተሳሰር ስራዎች
- ለሸማቾች መብት ጥበቃ ማህበር ድጋፍ የመስጠት ስራዎች
- የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ስራዎች ላይ የጥናት ስራዎችን መስራት
- የኮሚኒኬሽን ስራዎች

.

**የምክርና የህግ ድጋፍ ስራዎች**

- የሸማቹን ቅሬታዎች መቀበል የሚቻልበትን ግልጽ ስርኣት መዘርጋትና ቅሬታውን በመቀበል ድጋፍ ማድረግ
- ሸማቹ የደረሰበትን በደል ወደ ዳኝነት አካል አቅርቦ አስተዳደራዊና ፍትሃ ብሄራዊ እርምጃዎች እንዲወሰድ ምክርና ድጋፍ መስጠት
- ሸማቹ ህጋዊ መብቱን ለማስከበር ለፍርድ ቤቶች አቤቱታ ክስ ማቅረበ ማቅረብ እንዲችል ተገቢውን የህግ ምክር ድጋፍ ማድረግ
- ሸማቹ ለዳኝነት አካልና ለፍርድ ቤቶች ያቀረባቸው አቤቱታዎችና ክስ አፈጻጸም መከታተልና ለሸማቹ ተገቢውን ድጋፍ ማድረግ

***የሸማቾችን መብትና ጥቅም የማስጠበቅ ሥራዎች***

- ሸማቹ ስለሚገዛው ዕቃ ወይም አገልግሎት ጥራትና አይነት በቂና ትክክለኛ መረጃ /መግለጫ / ስለማግኘቱ መከታተልና ማረጋገጥ
- ሸማቹ ህብረተሰብ ከነጋዴው ለገዛው ዕቃ የተሰጠውን ዋስትና ማግኘቱን መከታተልና ማረጋገጥ፣

- ሸማቹ የዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ጥራት ወይም አማራቾጮችን በማየት የዋጋ ድርደድር በማድረጉ ምክንያት እንዲገዛ አለመገደዱን መከታተልና ማረጋገጥ
- በንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግብይት ምክንያት ለሚደርስበት ጉዳት መካሱን ማረጋገጥና መከታተል
- ማንኛውም ነጋዴ ስለሚሸጣቸው የንግድ ዕቃዎችና ስለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ መግለጫ ስለመለጠፉ መከታተልና ማረጋገጥ
- በንግድ ዕቃዎች ላይ የሚለጠፉ መግለጫዎች አስፈላጊውን መረጃ ያሟሉና ግልጽ መሆናቸውን መከታተልና መረጋገጥ
- የምርትና የአገልግሎት ዋጋ ዝርዝር በግልጽ በሚታይ ቦታ ስለመለጠፉና

  ስራ ላይ ስለመዋላቸው መከታተልና ማረጋገጥ

- ማንኛውም ነጋዴ ለሸጠው ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሸማቹ ደረሰኝ የመስጠት ግዴታ መወጣቱን ቀሪ መያዙን መከታተልና ማረጋገጥ
- ሸማቹ ህብረተሰብ ከንግድ ዕቃና ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚፈልገውን መረጃ ከነጋዴው መውሰድ ስለመቻሉ ማረጋገጥ
- ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በማንኛውም መንገድ የሚገለጹና የሚወጡ የንግድ ማስታወቂያዎች ሀሰተኛ ወይም አሳሳች አለመሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ
- ስለንግድ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በማንኛውም መንገድ የሚገለጹና የሚወጡ የንግድ ማስታወቂያዎች ሀሰተኛ ወይም አሳሳች አለመሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ
- በሸማችና በነጋዴዎች መካከል የሚደረጉ የዉል ግዴታዎች ሸማቹ በህግ ያሉትን መብቶች እንዳይጠቀም የሚከለክሉት ወይም ነጋዴው በአዋጅ የተጣለበትን ግዴታ የሚያስቀሩ መሆናቸውን መከታተል
- በማንኛውም ሰው ወይም ነጋዴ የሚፈጸሙ ተገቢ ያልሆኑና አሳሳች ተግባራትን መከታተልና መከላከል

**የመሰረታዊ ፍጆታ ዕቃዎች ስርጭትና የገበያ ዋጋ መረጃ ስራዎች**

- ለሸማቹ ህብረተሰብ በመንግስት ድጎማ የሚቀርቡ መሠረታዊ ሸቀጦች ስርጭት ፍትሃዊነት መከታተልና ማረጋገጥ
- በገበያ ውስጥ ያሉ የመሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ስርጭት ችግሮችን

  መለየትና የመፍትሔ አቅጣጫ ማስቀመጥ፣

- የገበያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማጠናቀር እና ማሰራጨት

☞ **የገበያ ልማትና ዘመናዊ የግብይት አስተዳደር ስራዎች**

**የገበያ ልማት ሥራዎች፤**

- የገበያ ፣የኤግዚቢሽንና ባዛር ማዕከላት ደረጃ መስፈርትና የአሰራር ስርዓትን የመዘርጋት ሰራዎች
- በክልሉ በተመረጡ ከተሞች ዘመናዊ የገበያ ማዕከላት የማቋቋም ስራዎች ፣

- የዘልማድ ገበያዎችን በማጥናትና እንደገና በማልማት የገበያ ተጠቃሚ ጥመርታን ያገናዘቡ እና ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎች ፣
- ነባር የገበያ ማዕከላት ቀጣይነታቸውን በማረጋገጥ በሚወጣላቸው ደረጃ መሰረት የውስጣዊ ዝግጅትና የመሰረተ ልማት ፍላጎትን እንዲያሟሉና ደረጃቸው እንዲሻሻል የማድረግ ስራዎች ፣
- ለገበያ የሚቀርቡ ምርቶችና አገልግሎቶችን ለማስተዋወቅ እና የገበያ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችሉ የኤግዚቢሽንና ባዛር ማዕከላት የማቋቋም ስራዎች፣
- የስልጠናና የኮሚኒኬሽን ስራዎች

**ዘመናዊ የግብይት አስተዳደር ሥራዎች**

- በየአስተዳደር እርከኑ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የነጋዴዎች ፎረም የማቋቋም ስራዎች
- የዘርፍ ማህበራት፣የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ምዝገባ ማድረግና ህጋዊ ሰውነት የመስጠት ስራዎች
- የኤግዚብሽንና የባዛር ፈቃድ የመስጠትና አፈጻጸሙን የመከታተል ስራዎች
- የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የነጋዴዎች ፎረምን የማጠናከር ስራዎች
- በንግዱ ዘርፍ የተሻለና ህጋዊ እንቅስቃሴ ለሚያደርጉ ግለሰቦች /ማህበራት የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋትን የመፈጸም ስራዎች
- በክልሉ የሚገኙትን ከፍተኛ መካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅቶች የማምረት አቅም እና የአቅርቦት መጠን አጠቃላይ መረጃ መዝግቦ የመያዝ፣ የመተንተንና የማሰራጨት ስራዎች
- ፍትሃዊ የግብይት ሥርዓት እንዲሰፍን ድጋፍ ለሚሹ የንግድ ተቋማት የሚታገዙበት ሁኔታ የማመቻቸት ስራዎች
- የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት ፣ የምርት ሥርጭት እና ውድድር እንዲኖር በመረጃ የተደገፈ የገበያ ትስስር ስርዓት የመፍጠርና የማስተግበር ስራዎች
- የገበያ ልማትና አስተዳደር ጥናታዊ ስራዎች
- የስልጠናና የኮሚኒኬሽን ስራዎች

## 7.የስራ ሂደቱ ስያሜና ትርጉም

### 7.1 ስያሜ

7.1.1. የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት

7.1.2 የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት

7.1.3 የገበያ ልማትና የግብይት አሰተዳደር ዋና የሥራ ሂደት

7.1.4 የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት

### 7.2 ትርጉም

**7.2.1 "የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት"** ማለት የኢትዮጵያ የንግድ ፈቃድ መስጫ መደቦችን መሰረት በማድረግ ተገልጋዩ ባቀረበው ጥያቄ መነሻ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ፤ ግልጽ፤ተደራሽ ፣ ፍትሃዊ እና ተወዳዳሪ የሆነ ህጋዊና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት መስጠት ነው፡፡

**7.2.2 "የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት "** ማለት በንግድ ስርዓቱ የሚከሰቱትን ህገ ወጥ የንግድ እንቅስቃሴ የመግታት፣በነፃ ገበያ ሥርዓት መሠረት ግልፅ፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋ እና ፍትሃዊ የማድረግ፣ የሸማቹንና የንግዱን ማህበረሰብ ሚዛናዊ ጥቅሞችን የማስጠበቅ እና ለሁሉም የንግድ ሥራ መስኮች ምቹ የሆነ የንግድ ስርዓት የማስፈን ተግባራትን መፈጸም ማለት ነው ፡፡

***7.2.3 "የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት" ማለት*** ሸማቹን ህብረተሰብ በግብይት ሂደት በሚፈጠሩ የጸረ- ውድድርና ተገቢ ያልሆነ የገበያ ተግባራት ምክንያት ከሚደርስበት ዘርፈ ብዙ ችግሮች የመጠበቅ፣ የመደራጀትና የመደራደር አቅሙን የማሳደግ ***እና*** በነጻ ገበያ ውድድር በሚመራው የንግድ አሰራር ውስጥ በተዘረጋው የዳኝነት ስርአት መብቱን የማስከበር ተግባራትን መፈጸም ማለት ነው ፡፡

**7.2..4 "የገበያ ልማትና የግብይት አሰተዳደር ዋና የሥራ ሂደት "** ማለት የግብይት ማዕከላትና የግብይት ስርዓትን መሰረታዊ በሆነ መልኩ የመቀየርና የማልማት፣ ዘመናዊ የንግድ ማዕከላትና ቀልጣፋ የአስተዳደር ሁኔታን የመፍጠር፣ ለግብይት የሚቀረበው ምርትና አገለግሎት ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን የማብቃት እንዲሁም የንግዱ ማህበረሰብን አቅም በመገንባት በውድድር ላይ የተመሰረተ የዳበረ የነጻ ስርዓት እንዲሰፍን የሚያስችሉ ተግባራትን የማከናወን ሂደት ነው።

8.የስራ ሂደት መለያ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ተልእኮ/mission/ | የሥራ ሂደቱ መጠሪያ/Process name/ | የሥራ ሂደቱ አይነት/Process type/ | የሥራ ሂደቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች/Process/ | ተገልጋይ Customer | ግብዓት Input | ውጤት output | የግብ ስኬት outcome |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ ልማትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ፡፡ | የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት | ዋና የሥራ ሂደት | • የንግድ ምዝገባ አገልግሎት<br>• የንግድ ስራ ፈቃድ አገልግሎት<br>• የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፈቃድ እድሳት አገልግሎት<br>• የንግድ ስራ ፈቃድ እገዳና ስረዛ<br>• የንግድ ማህበራት የመመስረቻ ጽሁፍ፣መተዳደርያ ደንብና ቃለጉባዔ ማጽደቅ<br>• የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዳታ ቤዝ በማዘጋጀት መረጃ ማስገባትና ማደራጀት፣መተንተንና ማሰራጨት<br>• የንግድ ምዝገባና ፈቃድመረጃዎችን በመረጃ መረብ መሰደር | ግለሰብ ነጋዴዎች የንግድ ማህበራት፤ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፤ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ አበዳሪ ተቋማት፤ ሸማች/ተጠቃሚው ህብረተሰብ፤ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች | የቀረበ ምዝገባ፣ ፈቃድ፣ዕድሳትና የመረጃ አገልግሎት ጥያቄ/ፍላጎት | የተሰጡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬቶች<br><br>የተሰጡ የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ ዕድሳት እና የተሰጠ መረጃ | ህጋዊነቱ በተረጋገጠና ዘመናዊ በሆነ የንግድ ምዝገባ፣ፍቃድ እና መረጃ አገልግሎት የተገነባ የንግድ ሥርዓት |

| ተ.ቁ | ተልእኮ/mission/ | የሥራ ሂደቱ መጠሪያ/Process name/ | የሥራ ሂደቱ አይነት/Process type/ | የሥራ ሂደቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች/Process/ | ተገልጋይ Customer | ግብዓት Input | ውጤት output | የግብ ስኬት outcome |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ ልማትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ፡፡ | የንግድ ኢንስፔክሽን ና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት | ዋና ስራ ሂደት | **የውስጥ ኢንስፔክሽን አሰራር**<br>የንግድምዝገባ፣ፍቃድ እና እድሳት በአግባቡ ስለመፈጸሙ<br>**ውጫዊ የኢንስፔክሽን አሠራር**<br>የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ኣድሳት ሳያደርጉበንግድ ስራ ላ\ይ በተሰማሩ ላይ የሚደረግ ኢንስፔክሽን<br>**የሬጉላቶሪ ስራዎች**<br>የህግ ማእቀፎችማስተባበርና አፈፃፀማቸውን መከታተል<br>የቴክኒክደንቦችማስተባበር/የፈቃድ መስጫመደቦችመስፈርቶችንየሚያወጡና የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጡ አካላትን ማስተባበር ፤<br>የንግድ ፈቃድ መስጫ መደቦችን በዝረዘር በማጥናት ለሚመለከተዉ አካል ማቅረብና ማስተግበር፤<br>የምርትና የአገልግሎት ጥራት ፍተሸ<br>የስነልክ መሳሪያዎች ካልቢሬሽንና ፍተሸ | ግለሰብ ነጋዴዎች፤<br>የንግድ ማህበራት፤<br>የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፤<br>የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፤<br>መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤<br>አበዳሪ ተቋማት፤<br>ሸማች/ተጠቃሚው ህብረተሰብ፤<br>ተማሪዎችና ተመራማሪዎች | **የኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ አገልግሎት ጥያቄ/ፍላጎት** | በፍትሀዊ የንግድ አሰራር የረካ ተገልጋይ | የሰፈነ ህጋዊና ፍትሀዊ ንግድ ስርዓት ፤ |

| ተ.ቁ | ተልእኮ/mission/ | የሥራ ሂደቱ መጠሪያ/Process name/ | የሥራ ሂደቱ አይነት/Process type/ | የሥራ ሂደቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች/Process/ | ተገልጋይ Customer | ግብዓት Input | ውጤት output | የግብ ስኬት outcome |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ ልማትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ። | የገበያ ልማትና የግብይት አስተዳደር የሥራ ሂደት | ዋና ስራ ሂደት | የገበያ ልማት ሥራዎች፤<br>በክልሉ በተመረጡ ከተሞች ዘመናዊ የገበያና የኤግዝቢሽን ማዕከላት ማቋቋም፣ ነባር የገበያ ማዕከላትን ማሻሻል እና የደረጃ መስፈርት ማውጣትና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤<br>ዘመናዊ የግብይት አስተዳደር ሥራዎች<br>በንግድ አሠራር እና በግብይት ሥርዓቱ ላይ የተለያዩ የጥናትና የምርምር ስራዎችን ማካሄድ ፣በንግዱ ማህበረሰብ የአደረጃጀትና የድጋፍ ሥራዎች እና የንግድ ስራ አመራር ስልጠና ሥራዎችን ማከናወን | ግለሰብ ነጋዴዎች፤ የንግድ ማህበራት፤ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፤ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ አበዳሪ ተቋማት፤ ሸማች/ተጠቃሚው ህብረተሰብ፤ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች | ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት የማስፈንና የገበያ ማዕከላት ልማት ጥያቄ /ፍላጎት / | ዘመናዊ የግብይት ስርአት በመዘርጋቱ የረካ ተገልጋይ | የተገነባ ምቹና ዘመናዊ የግብይት ስርአት |

| ተ.ቁ | ተልእኮ/mission/ | የሥራ ሂደቱ መጠሪያ/Process name/ | የሥራ ሂደቱ አይነት/Process type/ | የሥራ ሂደቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች/Process/ | ተገልጋይ Customer | ግብዓት Input | ውጤት output | የግብ ስኬት outcome |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት በማስፋፋት፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት በመዘርጋት የሸማቹንና የንግዱን ህብረተሰብ ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ ልማትንና መልካም አስተዳደርን ማረጋገጥ፡፡ | የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት | ዋና ስራ ሂደት | የሸማቾች መብት የማስጠበቅ፣ ግንዛቤ እና ተሳትፎ የማሳደግ ስራዎች<br>የሸማቾች ጥበቃ ህግ በአግባቡ መፈፀሙን መከታተልና ማረጋገጥ፤<br>ከሸማቾች የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መቀበልና ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግ<br>የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራትን የመደገፍ ስረራዎች<br>የትምህርትና ስልጠና ስራዎች<br><br>የምክርና የህግ ድጋፍ ስራዎች<br>የገበያ ዋጋ መረጃ ስራዎች | ግለሰብ ነጋዴዎች የንግድ ማህበራት፤ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች፤ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ አበዳሪ ተቋማት፤ ሸማች/ተጠቃሚው ህብረተሰብ፤ ተማሪዎችና ተመራማሪዎች፤ | **የሸማቹ መብት እንዲከበርና ተገቢ ጥያቄ/ፍላጎት** | • መብቱ የተጠበቀለት ተገልጋይ ና መብቱን ማጠበቅ የቻለ ሸማች | **የተገነባ የሸማቾች ጥበቃና መብቱን የሚያስጠብቅ ሸማች ህብረተሰብ** |

9.ዋና የሥራ ሂደት ለመምረጥ/ለመወሰን/ጠቃሚ የሆኑ ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | መልስ |
|---|---|---|
| 1 | ተቋሙ ከሌሎች ተቋማት ምን ምን የተለየ ስራ ይሰራል? | የንግድ ምዝገባ፣፣የንግድ ተቋም ዋስትና ምዝገባ የነንግድ የዘርፍ ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት የንግድ ስራ ፈቃድ፣ እድሳት፣ ስረዛ ማድረግ፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራር ማስፈን ፣ ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት ማደራጀትና ደረጃ ማውጣት፣ የሸማቾችን መብትና ጥቅም ማስከበር |
| 2 | ተቋሙ ለተገልጋዩ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ወይም ውጤቶች ውስጥ ለተገልጋይ ከፍተኛ ፋይዳ የሚሰጡ የትኞቹ ናቸው? | የተሰጡ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሰርተፊኬቶች ፣የተሰጡ የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ ዕድሳት ፣የሰፈነ ህጋዊና ፍትሀዊ የንግድ አሰራር ምቹና ዘመናዊ የግብይት ስርአት፣መብቱ የተጠበቀለት ተገልጋዩ እና በተሰጠው የዳኝነት አገልግሎት የረኩ ደንበኞች |
| 3 | ተቋሙ በብቸኝነት ወይም በተሸለ ሁኔታ የሚያከናውናቸውበመሆናቸው ለሌሎች ስራዎች ተላልፈው የማይሰጡ ስራዎች ምንድናቸው? | የንግድ ምዝገባ፣የንግድ ተቋም ዋስትና ምዝገባ፣ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፣የንግድ ስራ ፈቃድ፣ እድሳት፣ ስረዛ ማድረግ፣ የንግድ ማህበራትን መመስረቻ ና መተዳደርያ ደንብ ማጽደቅ/ማሻሻል/ የማህበራት አክሲዮን ሽያጭ ማጽደቅ፣የንግድ ማህበራት ቋለ ጉባኤ ማጽደቅ፣ የፍትሃዊ የንግድ አሰራር ማስፈን ፣ ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት ማደራጀትና ደረጃ ማውጣት፣ የሸማቾችን መብትና ጥቅም ማስከበር |
| 4 | ከተቋሙ ተልእኮና ህልውና ጋር የተያያዙ ወሳኞ ስራዎች ምንድናቸው? | የንግድ ምዝገባ፣፣የንግድ ተቋም ዋስትና ምዝገባ የነንግድ የዘርፍ ዘርፍ ማህበራት ምክርቤት የንግድ ስራ ፈቃድ፣ እድሳት፣ ስረዛ ማድረግ፣ፍትሃዊ የንግድ አሰራር ማስፈን ፣ ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት ማደራጀትና ደረጃ ማውጣት፣ የሸማቾችን መብትና ጥቅም ማስከበር |
| 5 | ከተገልጋይ መሰረታዊ ፍላጎት ወይም ጥያቄ በመነሳትና የተለያዩ የስራ ክፍሎች/ ተቋምን አልፎ ለተገልጋይ መሰረታዊ ፍላጎት ውጤት የሚሰጥ ሥራ? | የንግድ ምዝገባና የንግድ ስራ ፍቃድ ሰርተፍኬት መስጠት ፣ማደስና መሰረዝ የመረጃ አገልግሎት መስጠት ለቀረበ አቤቱታ ምላሽ መስጠትና ጥፋተኞች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ዘመናዊ የግብይት ማዕከላት |

## 10.1 የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድና መረጃ ዋና የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



10.2 የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



## 10.3 ሸማቾች ጥበቃ ዋና የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



## 10.4 የገበያ ልማትና ግብይት አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ



10. የሥራ ሂደት መምረጫ መስፈርት (Criteria )

| የሥራ ሂደት | በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለ/Dysfunctional/ | ለተገልጋይ ያለው ፋይዳና ከተቋሙ ተልዕኮ ጋር ያለው ከፍተኛ ቁርኝት/Importance/ | ተቻይነት/ Feasiblity/ |
|---|---|---|---|
| የንግድ ምዝገባ፣ፈቃድና መረጃ አገልግሎት<br>ዋና የሥራ ሂደት | • በወረዳና በክፍለ ከተማ ምዝገባና ፈቃድ ፈጻሚ አካል የክትትልና የቁጥጥር ስራም የሚፈጽም በመሆኑ ቼክና ባላንስ ማድረግ አለመቻሉ<br>• በ2000 ዓ/ም የተተገበረው BPR ከአዲሱ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ጋር ባለመጣጣሙ የአገልግሎት ስታንዳርድ መጠበቅ አለመቻሉ<br>• ነባሩ የሥራ ሂደት በክልሉ መንግስት የጸደቀውን የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራም ለማስፈጸም ምቹ አለመሆኑ<br>• ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና አሰረጫጨት ሥርዓት አለመኖሩ | ህጋዊነቱ የተረጋገጠና ዘመናዊ የሆነ የንግድ ምዝገባ፣ፍቃድ እና መረጃ አገልግሎት መስጠት ስለሚያስችል ከተገልጋዩ ፍላጎት አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑ<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራምን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችል በመሆኑ ህጋዊ ንግድ ለማስፈንና የሴክተሩን ተልዕኮ ለማስፈጸም ከፍተኛ ፋይዳ አለው | በስራ ላይ ከነበረው ቢፒአር የተገኘ ልምድና ተሞክሮ መኖሩ<br><br>የሰለጠነ በቂ የሰው ሃይል መኖሩ<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም የፕሮግራምና ምቹ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው |
| የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉለሽን ዋና የስራ ሂደት | • በወረዳና በክፍለ ከተማ ምዝገባና ፈቃድ ፈጻሚ አካል የክትትልና የቁጥጥር ስራም የሚፈጽም በመሆኑ ቼክና ባላንስ ማድረግ አለመቻሉ<br>• የህግ ማዕቀፎችንና የቴክንክ ደምቦችን አፈጻጸም ለመከታተልና ለማስተባበር የሚያስችል የአሰራር ሂደት አለመኖሩ | ፍትሀዊ የንግድ አሰራርንና ዘመናዊ የግብይት ስርአትን ለመዘርጋት ስለሚያስችል ከተገልጋዩ ፍላጎት አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ አለው<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራምን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችል በመሆኑ ህጋዊ ንግድ ለማስፈንና የሴክተሩን ተልዕኮ ለማስፈጸም ከፍተኛ ፋይዳ አለው | በስራ ላይ ከነበረው ቢፒአር የተገኘ ልምድና ተሞክሮ መኖሩ<br><br>የሰለጠነ በቂ የሰው ሃይል መኖሩ<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም የፕሮግራምና ምቹ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው |

10. የሥራ ሂደት መምረጫ መስፈርት (Criteria )

| **የሥራ ሂደት** | **በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለ/Dysfunctional/** | **ለተገልጋይ ያለው ፋይዳና ከተቋሙ ተልዕኮ ጋር ያለው ከፍተኛ ቁርኝት/Importance/** | **ተቻይነት/ Feasiblity/** |
|---|---|---|---|
| የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ ዋና የሥራ ሂደት | • የሸማቹን መብትና ጥቅም የሚያስከብር የአሰራር ሂደት አለመኖሩ<br>• አዲሱን የንግድ አሰራርና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ የሚያስፈጽም የአሰራር ሂደት አለመኖሩ | • ህጋዊ የንግድ አሰራርና ሸማቾች መብቱና ጥቅም ለማረጋገጥ ስለሚያስችል ከተገልጋዩ ፍላጎት አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ አለው<br>• የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራምን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችል በመሆኑ ህጋዊ ንግድ ለማስፈንና የሴክተሩን ተልዕኮ ለማስፈጸም ከፍተኛ ፋይዳ አለው | በስራ ላይ ከነበረው ቢፒአር የተገኘ ልምድና ተሞክሮ መኖሩ<br><br>የሰለጠነ በቂ የሰው ሃይል መኖሩ<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም የፕሮግራምና ምቹ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው |
| የገበያ ልማትና የግብይት አስተዳደር ዋና የስራ ሂደት | • የገበያ ማዕከላት አደረጃጀት ኋላቀርነትና አለመስፋፋት<br>• ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት የሚዘረጋ የአሰራር ሂደት አለመኖሩ<br>• የንግዱ ማህበረሰብ የማደራጀት፣የመደገፍና ተሳትፎአቸዉን የማሳደግ ወጥ የሆነ የአሰራር ሂደት አለመኖሩ | ዘመናዊ የግብይት ስርአትን ለመዘርጋት የገበያ ትስስርን ለመፍጠር ስለሚያስችል ከተገልጋዩ ፍላጎት አንጻር ከፍተኛ ፋይዳ አለው<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም ፕሮግራምን በተሟላ ሁኔታ ለማስፈጸም የሚያስችል በመሆኑ ህጋዊ ንግድ ለማስፈንና የሴክተሩን ተልዕኮ ለማስፈጸም ከፍተኛ ፋይዳ አለው | በስራ ላይ ከነበረው ቢፒአር የተገኘ ልምድና ተሞክሮ መኖሩ<br><br>የሰለጠነ በቂ የሰው ሃይል መኖሩ<br><br>የንግድ ሥርዓት ሪፎርም የፕሮግራምና ምቹ የህግ ማዕቀፎች መኖራቸው |

## 11. ማጠቃለያ

በመስፈርቱ የተመረጡ ወሳኝ የስራ ሂደቶች፤

11.1 የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድና መረጃ አገልግሎት ዋና የሥራ ሂደት

11.2 የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉሌሽን ዋና የሥራ ሂደት

11.3 የሸማቾች ጥበቃና ድጋፍ  ዋና የሥራ ሂደት

11.4 የገበያ ልማትና የግብይት አስተዳደር ዋና የሥራ ሂደት